**Dallas Office**
**4002 Blacksmith Dr**
**Garland, TX 75044**
**Tel: 813-312-1502**
Email: info@globalallianceforethiopia.org
Website: www.globalallianceforethiopia.org

# አ ቤ ቱ ታ

**እ.ኤ.አ. በ1935-'41 ኢትዮጵያ ላይ ስለ ተፈጸመ የጦር ወንጀል ተባባሪነቷ፤ የቫቲካን መንግሥት ይቅርታ እንድትጠይቅ**



እኛ፤ ከዚህ በታች ስማችንን በፊርማችን ያረጋገጥን፤ እ.ኤ.አ. በ1935-'41 ፋሺሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወርራ ባደረሰቺው አሰቃቂ የጦር ወንጀል፤ የቫቲካን መንግሥት እጅ ከኀንት ሆና ተባባሪ ስለ ነበረች፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ ተጽእኖ እንዲደረግባት፤ ለዓለም አቀፋዊው ሕብረተሰብ፤ በዓለም ላሉ መንግሥቶች ሁሉ፤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤ ለዓለም ቤተክርስቲያኖች፤ ለአይሑድ ምኩራቦች፤ ለመስጊዶች፤ ለሌሎች ለሚመለከታቸው ድርጅቶች እና ለእውነት ለቆሙ ሕዝቦች፤ ድጋፋቸውን እንዲያበረክቱ አቤቱታችንን በታላቅ ትሕትና እናቀርባለን።

የሙሶሊኒ ፋሺሽት ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ የእልቂት ዘመቻውን ለመፈጸም ከኢጣልያ ሲነሳ፤ በፖፕ ፓየስ 11ኛ ትመራ የነበረቺው ቫቲካን ቡራኬዋን ለግሳ ነበር። የፋሺሽቱ ጦርም፤ ከአንድ ሚሊዮን ያላነሱ ኢትዮጵያውያንን፤ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሳትን ጭምር፤ ጨፈጨፈ። 2000 ቤተክርስቲያኖችንና፤ 525 000 የመኖሪያ ቤቶችን ከማውደሙ በተጨማሪ በስነፍጥረት ላይ እጅግ የከፋ ጉዳት አድርሷል። በተፈጸሙት አሰቃቂ ድርጊቶች፤ በፋሺሽት አይሮፕላኖች በተረጨው የመርዝ ጋዝ ጭምር፤ ጦርነት በተከናወነባቸው ስፍራዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የገጠር አካባቢዎች፤ በተመረዘው አየር፤ ውሀ፤ በእጸዋትና በሰብሎች የተጠቀሙ ሰዎችና እንስሶች በብዛት አለቁ። ይህ ሁሉ እልቂት ሲፈጸም፤ ከአሁኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በፊት የነበረው የሐገሮች ሕብረት (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) የተሰኘው ተቋም እንዲሁም 52 የዓለም መንግሥታት እና የቫቲካን መንግሥት ራሷ ጉዳዩን እየተመለከቱ በዝምታ አለፉት።

ምንም እንኳ ሙሶሊኒ እ.ኤ.አ. በ1935-'41 ኢትዮጵያ ላይ ያከናወነው ጭፍጨፋ ሒትለር በአይሑዶች ላይ የሰው ልጅ ማጥፋት ወንጀል ባከናወነበት ዘመን ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው እልቂት በዓለም የታሪክ መጻሕፍት እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰው ልጅ ማጥፋት መዝገብ ውስጥ አልተጠቀሰም። ናዚዎች በአይሑዶች ላይ እልቂት ሲፈጽሙ የቫቲካን መንግሥት ዝም በማለቷ ብቻ በክርስቲያናዊ ትሕትና

አይሑዶችን ይቅርታ የጠየቀች ሲሆን ፋሺሽቶች ኢትዮጵያ ላይ ስላደረሱት ሰቆቃ የቫቲካን መንግሥት እጅ ከጓንት ሆና የተባበረች ቢሆንም እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይትርታ አልጠየቀቺም። የቫቲካን መንግሥት ዝምታ እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተፈጸመውን እልቂት ችላ ማለት፤ የሰብዓዊ መብቶችንና የፍትሕን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች የሚጻረር ድርጊት ከመሆኑ በላይ ለሁሉም ትውልድና ሕሊና ላላቸው ሰዎች በሙሉ፤ በተለይ ለአፍሪካውያን፤ አሳዛኝነቱ እየቀጠለ ነው።

የቫቲካን መንግሥት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤ በገለልታ ዘዴ ብትጠየቅም መልስ እንኳ አልሰጠቺም። ስለዚህ፤ ቫቲካን፤ ከፋሺሽቶች ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው እልቂት፤ የተሟላና ይፋዊ የሆነ ይቅርታ እንድትጠይቅ ይደረግ ዘንድ፤ ለዓለም-አቀፍ ሕብረተሰቡ ይህንን አቤቱታችንን እናቀርባለን።

ስም፤---------------------------------------------- አድራሻ፡ ___________________________________

___________________________________
----------------------------------------------------
----------------------------------------------------

ፊርማ፤ ______________________________ ቀን፤ ----------------------------------------------------

ኢ.ሜይል----------------------------------------------------